# የአውሬው ምልክት (666)

www.DivineRevelations.info/Amharic




## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አውሬው ምልክት ምን ይላል ?



የዮሐንስ ራእይ 13:15-18

የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፣ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ **በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፣ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቁጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል** ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፤ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና፣ ቁጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።

የዮሐንስ ራእይ 14:9-11

ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፣ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ :- ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፣ እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ **ሳይቀላቀል** ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፣ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሣቀያል። የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፣ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ **የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ** ቀንና ሌሊት እረፍት የላቸውም። (ማለትም 666)"

ይህ እንዴት እንደሚከናወን ብዙ አይነት ግምት አለ፤ ግን ይህንን እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ . . . የአውሬውን ምልክት 666 የተቀበለ ማንም በዘላለም ሞት ይፈረድበታል! **ወደኋላ መመለስ የለም፣ ምሕረት ማግኘት የለም፣ ሁለተኛ እድል ማግኘት የለም፣ ድህነት የለም፣ ከዚህም ኃጢአት መዳን (መንጻት) አይቻልም!**። እንዲህም ብላችሁ አታስቡ . . . *"እግዚአብሔር ይረዳል፣ የአውሬውን ምልክት ብቀበልም እርሱ ይቅር ይለኛል፣ እርሱ መሃሪ ነው፣ እርሱ ሕይወቴን እንዳጣ አይፈልግም። መስጋት (መጨነቅ) የለብኝም፣ እኔ አሁንም መዳን እችላለሁ፣ ትክክል አይደል?"* ***ስህተት ነው!!!*** ይህንን የአውሬውን ምልክት በግምባርህ ወይም በእጅህ ብትቀበል፣ አልቆልሃል (ተጠናቆልሃል)! አትድንም ! ለአውሬው ታማኝ መሆንህን አሳውቀሃል (ፈልገሃል)። ምልክቱ ይፋ በሆነ ጊዜ ታላቅ ጭንቀት እና መከራ(ችግር) ይሆናል። ምናልባትም ለመትረፍና ብዙ ችግሮችን ለመፍታት የበለጠ (ምርጥ) ነገርን ማድረግ የሚያስፈልግ ይመስላል። ምልክቱን እንድትቀበሉ ታላቅ ግፊት (ጫና) በእናንተ ላይ ይሆናል፣ ማለትም የስቃይ ቅጣት፣ ህይወትን ማጣት፣ ሥራን ማጣት፣ ልጆችን ማጣት፣ ንብረትን፣ ዝናን፣ ቤትን፣ ነፃነትን፣ እጅና እግርን፣ ወ.ዘ.ተ ማጣት። ሰይጣን ምልክቱን አልቀበልም ያሉትን በቀላሉ አንገታቸውን መቁረጥ አይፈልግም ብለው የእግዚአብሔር ነብያት አስቀድመው አስጠንቅቀዋል፣ ግን የሱን ምልክት እንዲቀበሉ በአሰቃቂ ሁኔታ ያሰቃያቸዋል። ያለ ምልክቱ ማንኛውንም ነገር መግዛትም ሆነ መሸጥ አትችሉም። በዛ ሠዓት ላይ፣ ምልክቱን ከመቀበል ይልቅ የግዴታ ለመሞት ዝግጁ መሆን አለባችሁ። ቅጣቱ ምንም ሆነ ምን፣ የአውሬውን ምልክት ከመቀበል ይልቅ የሞት ቅጣቱን ለመቀበል የግድ ዝግጁ መሆን አለባችሁ። አስታራቂ ሃሳብ አታቅርቡ፣ በነገሩ ላይም ምንም ስህተት አትስሩ፣ ምልክቱን የሚቀበሉ፣ አማኞች ቢሆኑም እንኳ፣ **በእግዚአብሔር ሙሉ ቁጣ ለዘለአለም ይፈረድባቸዋል!** እራስን ለማጥፋት መሞከር ከመከራውና ምልክቱን ከመቀበል ይታደገኛል (ያድነኛል) ብላችሁ አታስቡ። ራስን ማጥፋት አይታደጋችሁም (አያድናችሁም)፤ ወደ ሲኦል ያስገባችኋል፣ አማኞች ብትሆኑም እንኳ። ደግሞ፣ በኢየሱስ የማታምኑ ከሆናችሁ፣ ምልክቱን አለመቀበልም ብቻ አያድናችሁም። ኢየሱስን ማመንና መግለጽ፣ እና ምልክቱን እምቢ (አልቀበልም) ማለት የግድ አለባችሁ፣ ይህንን ስታደርጉ ብቻ ነው መዳን የምትችሉት። የአውሬውን ምልክት ያልተቀበሉት እና ስለ እምነታቸው ለተገደሉት፣ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ወደ ገነት ከመሄድ ቀርተው በዚህ ምድር ለቀሩት ግን አሁንም ተስፋ አላቸው።



የዮሐንስ ራእይ 20:4 **ዙፋኖችንም አየሁ፣ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው**



**የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።** Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmail.com